የተከበሩ አቶ ያለው አባተ!

የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ!

የተከበሩ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው!

የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት ፕሬዚዳንት!

የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!

ክቡራትና ክቡራን!

1. በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 116/2 ዋና ኦዲተር መ/ቤት የክልሉ መንግስት ተቋማትና የሌሎች መስሪያ ቤቶች ሂሳቦችን በመቆጣጠር በክልል ም/ቤት የተመደበው ዓመታዊ በጀት በበጀት ዓመቱ ውስጥ እንዲሰሩ ለተወሰኑት ስራዎች በሚገባ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሪፖርት ለምክር ቤቱ እንደሚያቀርብ ይደነግጋል፡፡
2. በዚሁ መሰረት መ/ቤቱ አዲሱን የኦዲት አሠራር (የኢንትሪም ኦዲት) እስከጀመረበት መጋቢት/2005 ዓ.ም ድረስ የ119 መ/ቤቶችን የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ አቅዶ የ123 (103%) ያከናወነ ሲሆን ከእነዚህም መካከል 15ቱ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች ናቸው፡፡ በዚህ ጉባኤ የቀረበው እስከ መጋቢት/2005 የተከናወኑ የ123 መ/ቤቶች የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ውጤትን የሚያሳይ ሪፖርት ብቻ ነው፡፡

   በ2005 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በአወቃቀር እርከን ሲታይ በክልል/ማእከል 27 (22%)፣በዞን 2(2%)፤በከተማ አስተዳደሮች 16(13%)፤ 78(63%) በወረዳ ደረጃ ያሉ ናቸው፡፡
3. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ሠራተኞችና ኃላፊዎች የሠጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከ3ኛ ወገኖች የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች በኦዲት ስራው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በኦዲት ስራውም አለም አቀፍ እና ብሔራዊ የኦዲት አሠራር መርሆዎችና ስታንዳርዶች ሥራ ላይ ውለዋል፤ አስተማማኝና ተጨባጭ ማስረጃዎችም ተገኝተዋል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበሩ ፕሬዚዳንት!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

ከዚህ ቀጥሎ በፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት የተደረሰበት የኦዲት አስተያየትና መልስ አሰጣጥ እንዲሁም ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችን አቀርባለሁ፡፡ ዝርዝር ሁኔታውን ይህ ሪፖርት ከተወሰደበት በርካታ ገጾችና አባሪዎች ይዞ ከተዘጋጀው አጠቃላይ ዘገባ መመልከት የሚቻል መሆኑን ከወዲሁ መግለጽ እወዳለሁ፡፡

መ/ቤቱ በሚያካሂዳቸው ኦዲቶች የሂሳብ መግለጫዎችን አዘገጃጅት፤አቀራረብ እና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ግድፈቶች እንዲሁም በአፈፃፀማቸው ከደንብና መመሪያ ወጣ ያሉ ሁኔታዎች ያጋጠሙ ቢሆንም በዚህ ሪፖርት የተካተቱት ለም/ቤቱ ሪፖርት ሊደረጉ የሚገባቸው አንኳር አንኳር ግኝቶች ብቻ ናቸው፡፡

**የኦዲት አስተያየት፤**

4. **የ2004** በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተ□ረጉ **123 መ/ቤቶች** ውስጥ **ለ101(82%)ከዚህ በስተቀር፣** ለ7 (5.7%) **አስተያየት መስጠት አልተቻለም፣** ለ2(1.6%)፤ **አጥጋቢ አይደለም** 10 (8%) **የልዩ ኦዲት ሥራ** በመሆናቸው የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠባቸውና 1(1%)አስተያየት መስጠት የማያስፈልገው በትብብር የተሰራ ሂሣብ ናቸዉ፡፡
5. ከ123 መ/ቤቶች ውስጥ 7(5.7%) መ/ቤቶች የገንዘብ አያያዝና አስተዳደሩም ሆነ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን መርምሮ ተዓማኒና በቂ የሂሳብ አያያዝና አስተዳደር መኖሩን ለማረጋገጥና ስለሂሳቡ ትክክለኛ መሆን አለመሆን የሙያ አስተያየት ለመስጠት ገደብ በመኖሩና ይህም ጉልህና መሰረታዊ ችግር በመሆኑ‹‹**አስተያየት መስጠት አልተቻለም**››የሚል የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷቸዋል፡፡ መ/ቤቶቹም፡-
    1. ደብረማርቆስ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፤
    2. ምዕራብ ጎጃም ዞን ማረሚያ ቤቶች መምሪያ፤
    3. ላይ ጋይንት ወረዳ ነ/ፋ/ደ/ስ/ማዕከል፤
    4. መተማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል፤
    5. በየዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል፤
    6. አይከል ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል፤
    7. ደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ናቸው፡፡
6. ከ123 መ/ቤቶች ውስጥ 2(1.6%) መ/ቤቶች **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው ሲሆኑ መ/ቤቶቹም፡-
    1. ተንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል እና
    2. ደጀን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ናቸው፡፡

**"አጥጋቢ አይደለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች መንግሥት የመደበላቸውን ሀብት ህጉ በሚፈቅደው አሰራር መሠረት ስራ ላይ ያላዋሉ፤የማጭበርበር ተንኮል የተፈፀመባቸው፤ጉልህና መሠረታዊ ግኝቶችና የአሰራር ችግሮች የተስተዋሉባቸው ናቸው፡፡

7. ከዚህ ውጭ ያሉት 103(83.7%) መ/ቤቶች በአንፃራዊ መልኩ በሪፖርቱ ውስጥ ጉልህ ቢሆኑም መሰረታዊ ያልሆኑና ተለይተው ከተገለጹት ግኝቶች በስተቀር በተነጻጻሪ የተሻለ የሂሳብ አያያዝና የመንግስት ገንዘብ አስተዳደር የታየባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡

   በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት የተሰጠዉ የኦዲት አስተያየት በ2005 በጀት ዓመት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር ሲነጻጸር **"አስተያየት መስጠት አለመቻል"** እና **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚለው በ5.7% መቀነስ ማሳየቱ የሂሣብ አያያዝ ስርዓቱ በአንጻራዊ ሁኔታ እየተሻሻለ መምጣቱን የሚያመላክት ሲሆን የኦዲት አስተያየት የማይሰጥበትና ከተለያዩ አካላት የቀረበን ጥቆማና ጥያቄ መሰረት በማድረግ የተሠራው የልዩ ኦዲት ሂሣብ ደግሞ በ50% መጨመሩ ማህበረሰቡ ከመ/ቤታችን ጋር በመቀናጀት ኪራይ ሰብሳቢነትን በመዋጋቱ በኩል ያለው ተሳትፎ መጨመሩን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል **"ከዚህ በስተቀር"** የሚለው አስተያየት በሁለቱም አመታት ተቀራራቢ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

## የኦዲት ሪፖርቶች መልስ አሰጣጥ፣

8. በበጀት ዓመቱ በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 113 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 13(12%) እና በልዩ ኦዲት ከተከናወኑት 8 መልስ ያልሰጡ ሲሆኑ ባለፈው ዓመት በተመሳሳይ ጊዜ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉ 144 መ/ቤቶች መካከል 17(12%) መልስ ካልሰጡት ጋር ሲነጻጸር መልስ አሠጣጡ በመደበኛው ተቀራራቢ ሲሆን በተለይ ለልዩ ኦዲት ውጤቶች ምላሽ የመሰጠት ዝግጁነቱ አናሳና አዝጋሚ ሆኖ ይታያል፡፡

**በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች** ውስጥ መልስ ያልሰጡ መ/ቤቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡-

1. በየዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፤
2. አዲአርቃይ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል
3. ጅሌ ጥሙጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፤
4. ደባርቅ ወረዳ /ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፤
5. ደባርቅ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፤
6. ቀወት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፤
7. አንጎለላና ጠራ ወ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፤
8. አንኮበር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፤
9. ዳንግላ ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፤
10. ሞጃና ወደራ ወ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፤
11. መርሳ ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት፤
12. ከሚሴ ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት፤
13. ማቻከል ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ናቸው፡፡

## የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፤

9. የ2004 በጀት ዓመት ሂሳባቸው በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት መካከል በ51 መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2004 ዓ.ም ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ሲሆን ዝርዝር ምክንያቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡-

   - የተሟላ የሂሳብ መዝገብ /ሌጀር/ ተዘጋጅቶ የሂሳብ ምዝገባ ያልተደረገና ትክክለኛውን ከወጪ ቀሪ ሊያመለክት ባለመቻሉ፣

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በካዝና የሚገኝ ጥሬ ገንዘብና እንደጥሬ ገንዘብ የሚቆጠሩ ሂሳቦች የተሟላና ህጋዊ ቆጠራ ባለመደረጉ፤
- ገንዘቡ በአንድ ገንዘብ ያዥ ተይዞ እየተዳደረ ባለበት ሁኔታ የውስጥ ገቢን ሳይጨምር የመደበኛ ጥሬ ገንዘብ ሂሳብን ብቻ ነጥሎ ቆጠራ የሚደረግ በመሆኑ፤
- በገንዘብ ያዥ የሥራ መደብ ላይ በርካታ ሠራተኞች እየተለዋወጡ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብን ያንቀሳቀሱ ሲሆን ርክክብ በተፈፀመበት ወቅት በገቢ ደረሰኞች፤ በወጪ ቫውቸሮችና በጥሬ ገንዘብ መከታተያ ሌጀሮች ላይ ርክክብ በተደረገበት ዕለት በጋራ በመፈራረም የመለያ (Cut-off) ምልክት ያልተደረገ መሆኑ እና ገንዘብ ያዦች በሚቀያየሩበት ወቅት ርክክብ ሲፈፀም የጥሬ ገንዘብ ሌጀር ከወጪ ቀሪ በቆጠራ እየተረጋገጠ ርክክብ የማይፈፀም መሆኑ፣
- ኦዲት አስደራጊዎች በኦዲት ወቅት የገቢና የወጪ ሂሣቡን መዝግበው እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ምዝገባውን አጠናቀው ለማቅረብ አለመቻላቸው፣
- የተለያዩ የፕሮጀክት ሂሣቦች ከወጪ ቀሪያቸውን የሚያሣይ መቆጣጠሪያ የጥሬ ገንዘብ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው ሆኖ መገኘቱ ነው።

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻሉባቸው ስለሆኑ መ/ቤቶቹ አሰራራቸውን እንዲያስተካክሉና በየጊዜውም በውስጥ ኦዲተሮቻቸው እየተከታተሉ የጥሬ ገንዘብ አያያዛቸውን እንዲያሻሽሉ በየሪፖርቱ አሳስበናል፡፡

10. የ2004 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በ5ቱ የቀድሞ ገንዘብ ያዦች የተቶኘ ጠቅላላ ጉድለት ብር 709,701.20 ሲሆን በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በሌሎች 7 መ/ቤት ብር 1,248,454.47 የሌጀር ከወጪ ቀሪ በቆጠራ ከተገኘው በመብለጥ (ጥሬ ገንዘብ በማነስ) መከሰቱ ተስተውሏል።

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ከታየባቸው መ/ቤቶችም፤

**የመሃል ሜይንት ወ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 555,546.33** ጉድለት መከሰት ዋና ዋና ምክንያቶች፤

- በካዝና የሚገኘው ጥሬ ገንዘብና የቅድሚያ ክፍያ ሠነድ የሂሳቡ ሌጀር (መዝገብ) ከሚያሣየው ከወጪ ቀሪ ጋር በየጊዜው እየተገናዘበ የጥሬ ገንዘብ ትክክለኛነት የማይረጋገጥና ቁጥጥር የማይደረግበት መሆኑ፤ገንዘብ ያዥም ይህን የቁጥጥር መላላት እንደመልካም አጋጣሚ ተጠቅመው የመንግስትን ገንዘብ ማጉደላቸው፣
- የውስጥ ቁጥጥሩ በላላበት ሁኔታ ገንዘብ ያዥ ከ4 ዓመት በላይ ያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ በውስጥ ኦዲተሮች ኦዲት አለመደረጉ ገንዘብ ያዥም ይህን ክፍተት በመጠቀም እምነት ማጉደላቸው ነው። ጉዳዩም በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ ተመስርቶበት በቀጠሮ ላይ መሆኑን ከተገኙ ግብረ- መልሶች መረዳት ተችሏል።

**የገለጎ ከተማ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት ለተከሰተው ጉድለት ምክንያት** ቀደም ሲል በተላለፈው የዋስትና መመሪያ መሰረት የስራ ባህሪያቸዉ ከገንዘብና ንብረት መያዝ ጋር ግንኙነት ያላቸዉ ሠራተኞች ለስራ መደቡ የሚመጥን ዋስትና ማስያዝና ከ2002 በፊት በነበረው መመሪያ መሰረት በየበጀት ዓመቱ ማሳደስ የነበረባቸዉ ቢሆንም በቀን 24/06/2000 ዓ.ም የገቢ ሰብሳቢና መጥሪያ አዳይ በመሆን የተቀጠሩት አንድ ሠራተኛ ዋስ ሣያቀርቡ ስራ እንዲቀጥሉ በመደረጉ በቆዩበት አጋጣሚ የተጣለባቸውን እምነት በማጉደል ብር 91,310.00 ዘርፈው እንዲሄዱ ምክንያት ሆኗል፡፡

**የጓሃላ ከተማ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት** የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢና ዋና ገንዘብ ያዥ የነበሩት ብር 52,720.51 በጉድለት የሚፈለግባቸው መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ለጉድለቱ መከሰት አስተዋጽኦ ያደረጉ ተጠቃሽ ምክንያቶች፡-

- ገቢ በማይመለከታቸው ሠራተኞች ማለትም በጥበቃ ሠራተኛ፣ በሂሣብ ሠራተኛና በኮንትራት በተቀጠሩ የጥበቃና የጽዳት ሠራተኞች እንዲሰበሰብ በማድረግ፣
- የሚሰበሰበው ገቢ በወቅቱ ማጠቃለያ ደረሰኝ ሳይዘጋጅለትና ወደ ካዝና (ባንክ) ገቢ ሳይደረግ ከ2 ዓመት በላይ በዕለት ገንዘብ ሰብሳቢዎችና በዋና ገንዘብ ያዥ እጅ መቆየቱ፣
- በማይመለከታቸው የተለያዩ ሠራተኞች የተሰበሰበው ገንዘብ በቀጥታ በማጠቃለያ የገቢ ደረሰኝ ለዋና ገንዘብ ያዥ ወይም ለባንክ አካውንት ገቢ (ፈሰስ) መደረግ ሲገባው ለሌላ የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢ በነጭ ወረቀት በመስጠት እንደገና የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢው ለዋና ገንዘብ ያዥ ገቢ እንዲያደርግና በሂደትም ጉድለቱን ለማድበስበስና ተጠያቂነትን ለማጥፋት ጥረት በመደረጉ፣
- በ2002 ዓ.ም የተጠቃለለውን ገቢ፣ በ2000 እና በ2001 ዓ.ም ገንዘብ የተሰበሰበበትን የገቢ ደረሰኝ በማጣቀስና በማተካካት በማጠቃለያ ገቢ ደረሰኝ በመትከል በቅርብ ጊዜ የተሰበሰበን ገንዘብ ለግል ጥቅም ለማዋል ጊዜ በመግዛት፣
- የሂሣብ እንቅስቃሴ መዝገብና ሌጀር ካርድ ባለማቋቋምና ምዝገባ ባለማከናወን ለጉድለቱ አመች ሁኔታን በመፍጠር ነው፡፡

ስለሆነም አጉዳይን በህግ ከመጠየቅ በተጨማሪ አሰራሩ ሊታረም እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበን ጉዳዩ ክስ ተመስርቶበት በስር ፍ/ቤቱ የጥፋተኝነት ውሳኔ ቢሰጥም ተከሳሽ ይግባኝ ብለው በጠቅላይ ፍ/ቤት በመታየት ላይ እንደሚገኝ ከደረሱን ግብረ መልሶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

11. ከቀድሞ ገንዘብ ያዦች በሚፈለገው ጉድለት ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እን□ሚቱባቸው በየሪፖርቱ አሳስበን ብር 7,480.55 (1%) የተተካ፣ ብር 608,266.84 (86%) በፍታብሔርና በወንጀል ክስ ሂደት ላይ እንደሚገኝና ብር 93,953.79 (13%) ገና ክስ ለመመስረት በክትትል ላይ ያለ መሆኑን ከተሰጠው ምላሽ መረዳት ተችሏል፡፡

**የገቢ ሂሳብ ኦዲት ውጤት፤**

**የማጭበርበር ወንጀል የተፈጸመበት ገቢና የተጭበረበረበት ስልቶች፣**

12. የመንግስት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ ተሰብስቦ ለታለመለት ዓላማ መዋል ያለበት ቢሆንም በ2004 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች መካከል በ7ቱ ብር 155,947.53 በተጭበረበረ መንገድ ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም፡-

- በገለጎ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ለመንገድ ማሰሪያ ከተሰበሰበው ገንዘብ በተዘረጋው አሠራር ስርዓት መሠረት ስራ ላይ እንዲውል በሚመለከታቸው ሳይወሰን በግለሰቦች ስም ወጪ ተደርጎ የተለያዩ የሥራ ኃላፊዎች ለሽልማትና ለቀን ሰራተኞች የተከፈለ በማስመሰል ለግል ጥቅማቸው ያዋሉት ብር 36,000.00፣በነጭ ወረቀት ተሰብስቦ ለማዘጋጃ ቤቱ ገቢ ሳይደረግ የቀረ የአገልግሎት ክፍያ ገቢ ብር 967.53፤ በቀበሌ አስተዳደሩ የተሰበሰበ የ96 የመኖሪያ ቦታ ምሪት ከአገልግሎት ክፍያ ተሰብስቦ ወደ ማዘጋጃ ቤቱ ገቢ ሳይደረግ የቀረ ብር 18,590.00 በድምሩ ብር 55,557.53 ለግል ጥቅም የዋለ ገቢ መገኘቱ፤
- በቻግኒ ከተማ አሰተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት በ2000፤በ2001 እና በ2002 የግብር ዘመን በአንድ የንግድ ዘርፍ የተሰማሩ ግብር ከፋይ ላደረጉት የንግድ እንቅስቃሴ ከተወሰነባቸው ግብር፣ታክስ፣ መቀጫ እና ወለድ ለየዓመቱ ብር 10,000.00 እንደከፈሉ ከግብር ፋይላቸው ላይ ከታሰረው የገቢ ደረሰኝ (2ኛ ኮፒ) ላይ በግልጽ ተመልክቶ እያለ ይኸው ደረሰኝ በፊደልም ሆነ በአሀዝ ተሰርዞ ብር 40,000.00 እንደከፈሉ አስመስሎ በመጻፍ በልዩነት የሚታየው ገንዘብ ብር 30,000.00 (ከ40,000-10,000) ለ3 ዓመታት በድምሩ ብር 90,000.00 ከግብር ከፋዩ እዳ ላይ እንዲቀነስ በማድረግ ገንዘቡ ለመንግስት ገቢ ሳይደረግ የማጭበርበር ድርጊት ተፈጽሞበትና ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡
- በደሴ ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢ የተሰበሰበ ልዩ ልዩ ገቢ ብር 10,180.00 ለዋና ገንዘብ ያዥ (ለባንክ) ገቢ ሳይደረግ ለግል ጥቅም የዋለ መሆኑ በኦዲት ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

13. በጠቅላላው ከተጭበረበረው ገንዘብ ላይ ምን ያህሉ ከሚመለከታቸው እንደተተካ የደረሰን ምላሽ ባለመኖሩ ሁኔታውን ማወቅ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው መ/ቤቶች ገንዘቡን ለማስመለስ እና ያጭበረበሩ ግለሰቦችን ተጠያቂ ለማድረግ ክትትሉ ሊጠናከር ይገባል እንላለን፡፡

**ያልተሰበሰበ (በውዝፍ)የሚገኝ ገቢ፤**

14. **የ2004** በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ **123** መ/ቤቶች □ሱስዓ በ**43**ቱ ብር 33,184,690.45 በገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳ□ሰበሰብ (በውዝፍ) ተገኝቷል፡፡ ያልተሰበሰበ የመንግሥት ገንዘብ ከሚታይባቸው ዞኖች መካከል ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ብር 21,775,980.45፤ሰሜን ጎንደር ዞን ብር **5,748,520.34**፣ ሰሜን ወሎ ዞን ብር 1,751,153.76

ምስራቅ ጎጃም ዞን ብር 1,406,516.72 እና አዊ ብሄረሰብ አስተዳደር ብር 1,305,883.94 ከፍተኛ ውን ድርሻ ይይዛሉ::

መንግሥት የበጀት ዓመቱን ሥራ ለማከናወን ዕቅድ የሚነድፈው ገቢ የመሰብሰብ ሥልጣን በተሰጣቸው መ/ቤቶች ተሰብስቦ ስራ ላ□□እንደሚውል በታሳቢነት ተ□ዞ መሆኑ ይታ□ቃል:: ስለሆነም በገቢ አሰባሰብ ላይ መንግሥት ያደረጋቸውን የገቢ ግብር ማሻሻያዎች በመጠቀም ገቢን በወቅቱ ለመሰብሰብ ተገቢው ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ ለየመ/ቤቶች በተላከው ሪፖርት ተገልጿል፡፡ ከዚሁ ውዝፍ ገቢ ላይ ብር 470,694.94(1.4%) ብቻ ስለመሰብሰቡ በተሰጠው የኦዲት ሪፖርት ግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን ሌላው 98.6% ስለመሰብሰብ አለመሰብሰቡ እስከዚህ ሪፖርት ጥንቅር ድረስ ማወቅ አልተቻለም፡፡

**ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍና የሥራ ገቢ ግብር፤**

15. በገቢ ግብር ህጉ እንደተመለከተው ከተወሰነ መጠን በላይ የሆነ የእቃና አገልግሎት ክፍያ ሲፈጸም ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ መሰሠብሰብ የሚገባው 2 ከመቶ የንግድ ስራ ትርፍ ግብር እንዲሁም ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ሲከፈል መሰብሰብ የነበረበት ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ስራ ግብር ከ47 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 190,521.97 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ገቢው ከየሚመ ለከታቸው ላይ ክትትል ተደርጎ እንዲሰበሰብ በየሪፖርቶቹ ካሳሰብን በኋላ ብር 1,463.64 (0.8%)ብቻ እንደተሰበሰበ ከግብረ መልሱ መረዳት የተቻለ ሲሆን ቀሪው 99.2% በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

**□ወጪ ሒሣብ ኦዲት ውጤት፣**

**የማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ እና ዘዴዎች፣**

16. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ3ቱ(2.4%) የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ብር 3,450,722.75 ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ ማጭበርበሩ የተፈጸመባቸው መ/ቤቶችም:-

**የቆቦ ጊራና ሸለቆ ልማት ፕሮግራም ጽ/ቤት፤**

16.1 በተመሳሳይ ደረሰኝ 2 ጊዜ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሳብ ብር 1,345,722.61፤

ለእያንዳንዱ ክፍያ መቅረብ ያለበት ራሱን የቻለ ቁጥር ያለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሊሆን ሲገባው ቻይና ጂኦ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ኢትዩጵያ ቅርንጫፍ) ከፕ/ጽ/ቤቱ ጋር በያዛቸው የስራ ውሎች መሠረት ክፍያ ሲጠይቅ አንድ ዓይነት ቁጥር ያለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ 2 ጊዜ በማሳተም ከመጋቢት 26/1999 እስከ ሰኔ 24/2003 ዓ/ም ድረስ ከፕሮ/ጽ/ቤቱ የሰበሰበውን ብር 1,345,722.61 የተጨማሪ እሴት ታክስ የመንግስት ገንዘብ ለግል ጥቅም ያዋለ ሲሆን ፕሮግራም ጽ/ቤቱም ይህን መከላከል ሲገባው መከፈሉ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

ስለጉዳዩ የፌደራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት መረጋገጫ እንዲሰጥ በደብዳቤ ተጠይቆ ኮርፖሬሽኑ አንድ ዓይነት ቁጥር በያዘ ደረሰኝ 2 ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ በመሰብሰብ የፈፀመው ህገ ወጥ ድርጊት መሆኑን በማረጋገጥ በኮርፖሬሽኑ አድራሻ በመገኘት ስለጉዳዩ ለመጠየቅ ጥረት ቢደረግም የሚመለከታቸው የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎች ሊገኙ ባለመቻላቸው ከባለስልጣኑ መ/ቤት ጋር በመነጋገር ድርጅቱ ታሽጎ በታክስ ኦዲተሮች ልዩ ምርመራ እንደሚከናወንና ውጤቱንም በቀጣይ እንደሚያሳውቅ በቁጥር 5.1.0/1737/59 በቀን 19/3/2005 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ገልጾልናል፡፡ እንዲሁም፤

**16.2 ከፕ/ጽ/ቤቱ ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ ሳይደረግ የቀረ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 996,990.70፤**

በተጨማሪ እሴት ታክስ የተሰበሰበ ገንዘብን በቀጣዩ ወር ለግብር ሰብሳቢው ተቋም አሳውቆ መክፈል እንደሚገባ በታክስ ህጉ ላይ ቢደነገግም ይህን በመተላለፍ ቻይና ጅኦ ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን (ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ) ከጥር 25/2002 እስከ ሰኔ 24/2003 ዓ.ም ድረስ ከፕሮግራም ጽ/ቤቱ የሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 996,990.70 ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ህዳር 20/2005 ዓ.ም ድረስ ለመንግስት ገቢ እንዳላደረገ በፌደራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት በቁጥር ምዕ/3.2.2/2/3596 በቀን 20/3/2005 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ አረጋግጧል፡፡ በዚሁ የባለስልጣኑ ማረጋገጫ መሠረት ኮርፖሬሽኑ እስከ ታህሳስ/2002 ዓ.ም ድረስ የሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ብቻ ገቢ ማድረጉን አመልክቷል፡፡

ስለሆነም "ቀጣይ የክፍያ የምስክር ወረቀት ጸድቆ የሚከፈለው ቀድሞ የተከፈለው ታክስ በህግ በተቀመጠው መሰረት በወቅቱ ለመንግስት መከፈሉ ማረጋገጫ ሲቀርብ ብቻ ነው" በሚል የኢፌዴሪ የመሰረተ ልማት ሚኒስተር በቁጥር 296/መድ-44 በቀን መጋቢት 30/1995 ዓ.ም በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች ስራ ላይ እንዲውል ያስተላለፈውን መመሪያ ጠብቆ የመስራትና ይህን የማረጋገጥ ኃላፊነት የፕሮግራም ጽ/ቤቱ የቀድሞ ስራ አመራሮች ሆኖ እያለ ይህን ሳያደርጉና አንድ አይነት ቁጥር በያዘ ደረሰኝ ሁለት ጊዜ ክፍያዎች እንዲፈጽሙ ተዘጋጅቶ የቀረበውን ክፍያ በመፍቀድ የመንግስት ገንዘብ ለግብር አስገቢው አካል ሳይገባ እንዲቀር አድርገዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑም አንድ ዓይነት ቁጥር የያዘ ደረሰኝ 2 ጊዜ አሳትሞ በተለያዩ ጊዜዎች ለክፍያ በማቅረብና ታክሱን ሰብስቦ ለሚመለከተው ገቢ ባለማድረግ ከፈፀመው ህገ ወጥ ተግባር በተጨማሪ ለአንድ ዓመት ተኩል (ከጥር 25/2002-ሰኔ/2003 ዓ.ም) ከፕ/ጽ/ቤቱ የሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ እስከ ህዳር 20/2005 ዓ.ም ድረስ ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ አካል ገቢ ሳያደርግ በማቆየቱና የተጣለበትን ግዴታ ባለመወጣቱ ክትትል ተደርጎበት በህግ ሊጠየቅና ገንዘቡንም ገቢ ሊያደርግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

16.3 ሰነድ በመሰረዝና በመደለዝ ተጭበርብሮ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ብር 158,850.00፤

በክልሉ መስከረም 2001 ዓ.ም በወጣው የግዥ መመሪያ መሰረት የተሸከርካሪ ግዥ መከናወን ያለበት በንግድና ትራንስፖርት ቢሮ በኩል ወይም ቢሮው እንዲያውቀው ተደርጎ ውክልና ሲሰጥ መሆኑን መመሪያው የሚያዝ ቢሆንም ፕ/ጽ/ቤቱ ይህን በመተላለፍ በራሱ ስልጣን ህጋዊ አሰራርን ባልተከተለ መንገድ ቀጥታ የሞተር ብስክሌት ግዥ አከናውኖ ተገኝቷል፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ የተመረጠው አቅራቢ ድርጅት በጨረታ ሰነድ የተመለከተውንና ተወዳድሮ ያሸነፈውን ሞተር ሳይክል (TVS 160cc) ለማቅረብ እንዳልቻለ ገልፆ በ23/10/2003 ዓ.ም ለፕሮግራም ጽ/ቤቱ የላከው ደብዳቤ ቀን ተደልዞ፤

- በላዩ ላይ 20/10/2003 ዓ.ም የሚል ቀን የተፃፈበትና ደብዳቤው ለፕሮግራም ጽ/ቤቱ ገቢ የተደረገው ግን በ23/10/2003 ዓ.ም መሆኑ፤
- በቀረበው ጥያቄ ላይ የጨረታ ኮሚቴው የውሳኔ አስተያየት እንዲያቀርብ ከወቅቱ ስራ አስኪያጅ የተመራው በ24/10/2003 ሆኖ እያለ የጨረታ ኮሚቴው የውሳኔ አስተያየት ቃለ ጉባኤ ተሰርዞ በ23/10/2003 ዓ.ም እንዲሆን መደረጉ፤
- የፕሮግራም ጽ/ቤቱ መካኒክ ስለ ጥያቄውና ተለዋጭ የሞተር ሳይክል ሁኔታ የሙያ አስተያየት በ23/10/2003 ሰጥቶበት እያለ፤ የማኔጅመንት ኮሚቴው ቀደም ሲል በ20/10/2003 ዓ.ም በጨረታ ለተመረጠው ሞተር ሳይክል የተያዘውን የውሳኔ ሃሳብ ቃለ ጉባኤ በመደለዝ በ23/10/2003 ዓ.ም አድርጎ ማስተካከሉ፤
- ግዥው አስቀድሞ በጨረታ ውድድር ከተመረጠውና የጨረታ ዋጋው ከታወቀው ዓይነት ሞተር ሳይክል ውጭ በውድድሩ ወቅት መስፈርቱ (ስፔስፊኬሽኑ) ያልተገለጸ፤ በተጫራቾች በአማራጭ ያልቀረበና ዋጋው ያልታወቀውን እንዲሁም የዋጋ ጥናት ሳይካሄድ በቲ.ቪ.ኤስ 160ሲ.ሲ. ሞተር ሳይክል ፈንታ ሊፋን 200 ጂ.ዋይ-2 በተመሳሳይ ዋጋ እንዲቀርብ አላግባብ በመፍቀድ የተፈጸመው ህገ ወጥ ግዥ ከመሆኑም በተጨማሪ ዋጋው የተጋነነና ይህን ለመሸፋፈን ሰነድ የመደለዝ ስራ የተፈጸመበት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

በአሸናፊው ድርጅት አድራሻ አዲስ አበባ በመሄድ ስለሁኔታው ከአቅራቢው ድርጅት ለማጣራት ተሞክሮ በአድራሻው ተፈልጎ በአካል ሊገኝ አልቻለም፡፡

ኦዲት አስደራጊዎቹ ስለ ግዥው አፈጻጸም ዝርዝር ሁኔታ እንዲያስረዱ ኦዲት አስደራጊዎች ሲጠየቁ የፕሮግራም ጽ/ቤቱ መካኒክ ከአቅራቢው ድርጅት ድረስ በአካል በመገኘት ሞተር ብስክሌቱን ተመልክቶና ፈትሾ የተሻለ አቅም ያለውና ጽ/ቤቱንም የማይጎዳ መሆኑን አረጋግጧል በሚል 6 ሞተር ብስክሌት የአንዱ ዋጋ ብር 53,475.00 በድምሩ ብር 320,850.00 እንዲገዛ መደረጉን የጨረታ ኮሚቴው አባላትና በወቅቱ ስራ አስኪያጅ የነበሩት ገልጸዋል፡፡

ሆኖም በቀረበው ጥቆማ መሰረት ሞተር ብስክሌቶቹ የተገዙበት ዋጋ ትክክለኛነት ለማጣራት በተደረገ ጥረት ግዥው በተፈጸመበት ወቅት የሊፋን 200 ጂ.ዋይ-2 ሞተር ብስክሌት ያንዱ ዋጋ ከነቫቱ ብር 27,000.00 እንደነበር ከሊፋን ሞተር አጠቃላይ አስመጪ ድርጅት በቀን 10/3/2005 በቁጥር GT/03/297 በተፃፈ ደብዳቤ ከተገኘ የሰነድ ማረጋገጫ ጋር ሲነጻጸር (ከብር 53,475.00 ሲቀነስ ብር 27,000.00) በልዩነት በአንድ ሞተር ሳይክል ብር 26,475.00 በ6 ሞተር ሳይክሎች ደግሞ ብር 158,850.00 በተጭበረበረ ሁኔታ ያለ ህጋዊ ስልጣንና በተጋነነ ዋጋ መገዛቱ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም የመንግስት ገንዘብ ይህንኑ ከወሰኑ የፐ/ጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ተመላሽ ሆኖ ለፈጸሙት ተግባርም በህግ ሊጠየቁ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

በዚሁ መሰረት የስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን በየትኛው ግኝት ላይ ክስ መስርቶ እንዳስወሰነ በግረ መልሱ በዝርዝር ባይገልጽም በጥቅሉ እንደገለጸው ከሆነ የቀድሞ ስራ አስኪያጅ የነበሩት 13 ዓመት ፅኑ እስራትና ብር 50,000.00፤ሌሎች 2 የማኔጅመንት አባላት ከ9 እስከ 10 ዓመት ፅኑ እስራትና ከብር 30,000.00 እስከ ብር 45,000.00 የቅጣት ውሳኔ እንዳገኙና በሌሎች ጉዳዮች ላይም ክትትል እየተደረገ መሆኑን በጥቅል ከተሰጠው ግብረ-መልስ መረዳት ተችሏል፡፡

**አይከል ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል፤**

17. በ2002 በጀት ዓመት ግዥ ተፈጸመ ተብሎ በማጭበርበር ለግል ጥቅም የዋለ የግንባታ እቃ እና የነዳጅ ግዥ ሂሳብ ብር 700,129.70 የተገኘ ሲሆን ዝርዝሩ፡-

- ቆርቆሮ በቆርቆሮ ለተሰራው ቢሮ በከተማ አስተዳደሩ መሃንዲስ ተገምቶ በቀረበው የግንባታ ስራ ልኬታ መሰረት ከተገዛው 1857 ኩንታል ሰሚንቶ ስራ ላይ የዋለው 163 ኩንታል ብቻ በመሆኑ በልዩነት 1694 ኩንታል ያንዱ ዋጋ ብር 344.00 ጠቅላላ ዋጋ ብር 582,736.00 እና ለዚሁ ስራ የተገዛው ቆርቆሮ 1100 ሲሆን ስራ ላይ የዋለው 283 ብቻ በመሆኑ በልዩነት 817 ያንዱ ዋጋ ብር 94.00 ጠቅላላ ዋጋ ብር 76,798.00 እንዲሁም፤
- ነዳጅ እንደተገዛ የማስመሰያ ማስረጃዎችን (የሃሰት ፋክቱር) በማቅረብ ሂሳብ የተወራረደ ሲሆን ነዳጁ ወደ ጽ/ቤቱ ያልመጣና በአጠቃላይም ለጽ/ቤቱ አገልግሎት ሳይውል ገንዘቡ ወጪ ሆኖ ለግል ጥቅም የዋለ የነዳጅ ሂሣብ ብር 40,595.70፤

  በድምሩ ብር 700,129.70 ዋጋ ያለው ስሚንቶ፣ ቆርቆሮና ነዳጅ እንዲሁም የመጠንና ዋጋ ግምቱ በትክክል ያልታወቀ ሚስማር ለግል ጥቅም መዋሉ በተደረገው ኦዲት በማስረጃ በመረጋገጡ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪና የፍትህ አካላት ባሳወቅነው መሰረት በጉዳዩ ላይ ክስ ተመስርቶ በቀጠሮ ላይ ያለ መሆኑን ከተሰጠው ግብረ መልስ መረዳት ተችሏል፡፡

**ደብረ ማርቆስ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ፤**

18. ኮሌጁ ከሲዊዲን አገር መጡ ያላቸው ኮምፒውተሮች በአገልግሎት አሠጣጣቸው ችግር የታየባቸውና በርክክብ ወቅትም መስፈርታቸውን ያልጠበቁ ስለመሆናቸው በቀረበ ጥቆማ መነሻ መሠረት ጉዳዩን ለማጣራት ኮምፒዩተሮቹ ከሲዊድን አገር ስለመግባታቸው አንዳችም ማስረጃ ሊቀርብ ባለመቻሉ ይህንኑ እንዲያረጋግጥልን የፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በደብዳቤ ተጠይቆ 431 ዴስክ ቶፕ ኮምፒዉተሮች ብቻ በጉምሩክ በኩል ህጋዊና ከቀረጥ ነጻ ሆነው ከዉጭ የገቡ መሆናቸዉን በቁጥር አቃጉ23/እ58/05 በቀን 06/02/05 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ያረጋገጠልን ሲሆን በኮሌጁ በኩል ከሲዊዲን ሃገር ከቀረጽ ነጻ ገብተዋል በማለት ክፍያ ከፈጸመባቸው 476 ኮምፒዉተሮች ጋር ሲነጻጸር በልዩነት የሚታየዉ 40 ዴስክ ቶፕና 5 ላፕቶፕ በድምሩ 45 ኮምፒዉተሮች ከውጭ (ከሲዊድን) አገር አለመምጣታቸዉ ተረጋግጧል፡፡

ከኮሌጁ ጋር ውል የያዘው ኮምፒዩተር አስመጪው አካል በህጋዊ መንገድ ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገባ በመንግስት ለተፈቀደለት 431 ዴስክቶኘ ኮምፒዉተሮች ከሲዊድን አገር እስከ ደብረ ማርቆስ የማጓጓዣና ተያያዥ ወጪዎች ለአንድ ዴስክቶፕ ኮምፒዩተር ብር 3,000.00 (3000 ሲባዛ በ431) ሂሳብ በድምሩ ብር 1,293,000.00 ብቻ በኮሌጁ በኩል ክፍያ መፈጸም እንዳለበት በዉል ሰነዱ ላይ ተመልክቷል፡፡

ሆኖም ከውጭ አገር እንደመጡ በማስመሰል በሀገር ዉስጥ የት እንደተገኙ ያልታወቁ 40 ዴስክ ቶፕና 5 ላፕቶፕ ኮምፒዉተሮችን አብሮ በማስረከብ በድምሩ ለ476 ኮምፒዉተሮች ብር 1,438,000.00 የመጓጓዣያና ሌሎች ወጪዎች ክፍያ በመፈጸሙ ምክንያት በብልጫ ብር 145,000.00 (5 ላፕቶፕ ሲባዛ በብር 5,000.00) ሲደመር (40 ዴስክቶፕ ሲባዛ በብር 3,000.00)) ከውጭ ባልተጓጓዙ 45 ኮምፒዩተሮች ስም ወጪ ሆኖ ለግል ጥቅም ውሏል፡፡

የተከፈለው የመጓጓዣና ተያያዥ ወጪ ሆኖ ሳለ እንደ መግዣ ዋጋ በመቁጠርና ኮምፒውተሮቹም በትክክል አገልግሎት እየሰጡ እንደሆነ በመውሰድ‹‹መንግስትና ህዝብን የጎዳ ነገር የለም››በሚል እና ‹‹የኢፌዴሪ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተሳሳተ የዕቃዎች ገቢ ማስረጃ ሊሰጥ ይችላል›› በሚል ያልተረጋገጠ ምክንያት የክልሉ ፍትህ ቢሮ ክስ ከመመስረቱ በፊት ፋይል አያስከፍትም ብሎ መዝጋቱን ቢገልጽም የፌደራል ገቢዎችና ጎምሩክ ባለስልጣን በህጋዊ ደብዳቤ ያረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ከውጭ እንደመጡ የሚያሳይ ጉምሩክ ዲክላራሲዎንና ሌሎች መሰል ተጨባጭ የሰነድ ማስረጃዎች በኮሌጁ ባልቀረቡበት ሁኔታ እንዲሁም መስፈርታቸውን ያልጠበቁና ተገቢውን አገልግሎት እየሰጡ ባልሆኑ ኮምፒዩተሮች ‹‹መንግስት አልተጎዳም›› በሚል በፍትህ ቢሮ በኩል በጉዳዩ ላይ ክስ ተመስርቶ ክርክር ሳይደረግበት ከወዲሁ አያስከስስም መባሉን አግባብ ነው ብሎ መ/ቤታችን አልተቀበለውም፡፡

በመሆኑም የተፈጸመው ክፍያ ኮምፒዩተሮች ከሲዊድን እስከ ደብረ ማርቆስ ማጓጓዣና ተያያዥ ወጪ በሚል እንጅ የመግዣ ዋጋ ባለመሆኑና አስቀድሞ በውሉ ላይ በተቀመጠው መስፈርት (ስፔስፊኬሽን) መሰረት የመጡ ባለመሆናቸው የአገልግሎት መስጠት ችግር እንዳለባቸው ከኮሌጁ የተለያዩ የስራ ክፍሎች ባለሙያዎችና ኮምፒውተሮች ከተሰራጨላቸው ሌሎች ተመሣሣይ ኮሌጆች በተገኘ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

ይህም የህዝብንና የመንግስትን ጥቅም የሚነካና በማጭበርበር ለግል ጥቅም የዋለ በመሆኑ “ክስ አያስመሰርትም››መባሉ አግባብ አለመሆኑንና እንደገና መታየት እንዳለበት በመጥቀስ ለክልሉ ፍትህ ቢሮና ለስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በደብዳቤ ያሳወቀን ሲሆን ይህንን አስመልክቶ ኮሚሽኑ ጉዳዩን ለባለሙያ መርቶ በምርመራ ላይ እንደሚገኝ ገልጿል፡፡

**ደጀን ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል፤**

19. በውህድ ማምረቻ ላይ የሚሠሩ የቀን ሠራተኞች ሥራ ላልሠሩባቸው (እሁድ) ቀናት አሠሪ ኃላፊዎች ሀሰተኛ የሠዓት መቆጣጠሪያና መክፈያ ሰነድ (ፔሮል) ማስረጃ በማዘጋጀት ገንዘብ ለሠራተኞች ሣይሰጥ እንደተከፈለ አድረጎ በወጪ በመያዝ እንዲሁም ከውህድ ማምረቻው ሥራ በለቀቁ 9 ሠራተኞች ስም በስራ ላይ እንዳሉ ለማስመሰል የሠዓት መቆጣጠሪያ ሰነድ ተዘጋጅቶና ለሠራተኞች ክፍያ እንደተፈፀመ ተደርጎ በድምሩ ብር 53,024.20 በውህድ ማምረቻው ስራ አስኪያጅ ለግል ጥቅም መዋሉ በኦዲት በመረጋገጡ አስፈላጊው ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ ባሳሰብነው መሰረት ጉዳዩ በባለሙያ ተይዞ እየተመረመረ እንዳለ ከፍትህ አካላት ከተገኘ ግብረ መልስ መረዳት ተችሏል፡፡

**ገለጉ ከተማ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት፡**

20. የንዑስ ማዘጋጃ ቤቱ ሥራ አስኪያጅና አመራሮች በመመሳጠር እና ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም በቀን ሠራተኛ እና በጥበቃ ሰራተኛ ስም (መጻፍና ማንበብ በማይችሉ) በተጭበረበረ መንገድ ገንዘቡ ሣይከፈል እንደተከፈለ በማስመሰል በድምሩ ብር 51,005.54 የመንግስት ገንዘብ ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ ድርጊቱን በፈፀሙት ኃላፊዎች ላይም ተገቢው ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድባቸው እንደሚገባ ለፍትህ አካላት አሳውቀን ጉዳዩ ለባለሙያ ተመርቶ እየታየ እንደሆነ ከተሰጠው ግብረ መልስ መረዳት ተችሏል፡፡

ከተጭበረበረዉ የመንግስት ገንዘብ ተመላሽ የተደረገ ስለመኖሩ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጥቅምት 20/2006 ዓ.ም ድረስ ጉዳዩ በሂደት ላይ በመሆኑ ውጤትን ማወቅ አልቻልንም፡፡

በ2004 በጀት ዓመት ማጭበርበር የተፈጸመበት ክፍያ ብር 3,450,722.75 በ2003 በጀት ዓመት ከተጭበረበረው ብር 251,478.15 ጋር ሲነፃፀር የበጀት ዓመቱ በብር 3,199,244.60 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ ይህም አንዳንድ ሃላፊነታቸውን ላልተገባ ተግባር በሚያውሉና እምነት በሚያጎሉ ግለሰቦች

ላይ የፋይናንስ ተጠያቂነት ይበልጥ ካልተጠናከረ አዝማሚያው አስጊ ስለሆነ ትኩረት ሊደረግበት ይገባል፡፡

**ከሴክተር መ/ቤቶች ላይ ተወስዶ ለሚመለከተዉ ፈሠስ ሳይደረግ የቀረ ተጨማሪ እሴት ታክስ፤**

21. በ20 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 6,751,851.13 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት እንዲሁም በ13 መ/ቤቶች ብር 6,625,866.86 ያለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

   ገንዘቡ በወቅቱ ፈሠስ መደረጉን ክትትል ባለመደረጉ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ተሰብስቦ ለረዥም ጊዜ በሰብሳቢዎቹ እጅ እየተያዘ ለስራ ማስኬጃ የሚውልበትና ከጊዜ ብዛትም ፈሰስ የማይደረግበት ሁኔታ ከመኖሩም በላይ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የተከፈለዉ ደግሞ ታክሱ ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ የሚያስገድድ የመቆጣጠሪያ ስልት ስለማይኖረው ምን ጊዜም ሊሰበሰብ ስለማይችል አፈፃፀሙ የመግስትን ገንዘብ በማጭበርበር ከተጠቃሚው (ከከፋዩ) በመንግስት ስም ሰብስቦ ለግል ጥቅም በማዋል እንዲሁም በሌሎች ዜጎች ላይ ኢፍታዊ የገበያ ውድድር በመፍጠር በደል የሚደርስ በመሆኑ ለፈውን ትኩረት በመስጠት እንዲሰበሰብ ለወደፊቱም በክልል ደረጃ የተጀመረው የመንግስት ተቋማት ታክስን ቀንሶ የማስቀረት አሠራር እስከ ታችኛው አደረጃጀት ድረስ እንዲወርድ በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

**ለግል ጥቅም የዋለ የወጪ ሂሣብ፤**

**22. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች መካከል፡-**

22.1 በራያ ቆቦ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 196,427.29 ነባር የመጠጥ ውሃ ግንባታ ሥራዎች (ስትራክቸሮች) በአዲስ እንደተሰሩ ተደርጎ ርክክብ በመፈፀሙ በሰ/ወሎ ዞን ውሃ ሃብት ልማት መምሪያ ባለሙያዎች በተደረገ ጥናታዊ ግምገማ እንዲሁም በኦዲት ወቅት በአካል እንደተረጋገጠው እና በየጎጡ የሚገኙ የውሃ ኮሚቴዎች እና የአካባቢው ተጠቃሚዎች ባረጋገጡት መሰረት፣

- በአዲስ ያልተገነቡ ነባርና ጥገና የማይፈልጉ ሥራዎች (ስትራክቸሮች) ቦታ ርክክብ ላይ በአዲስ መልክ እንዲሰሩ መታዘዙ፣
- የውሃ ግንባታ ዝርዝር ሥራዎችን (ስትራክቸሮችን) አዲስ ለማስመሰል ውጫዊ ግንባታቸውን በስሱ በመለሰን የማሳሳቻ ሥራዎች በመከናወናቸው፤
- የወረዳው አመራር በቀን 29/04/04 ዓ.ም በተያዘ ቃለ-ጉባኤ ያሳለፈው ውሣኔ እንደሚያመለክቴው ‹‹የረጅ ድርጅቱ ሂሣብ እስከ ጥር 10/2004 ዓ.ም ድረስ ተወራርዶ መዘጋት እንዳለበት ካልሆነ ግን በጀቱ ይመለሳል፣ተጨማሪም አይለቀቅልንም፤ ሥራው ሳይከናወን የክፍያ የምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ ርክክብ በየጎጡ ተፈፅሞ እና ሌሎች የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ሂሳቡ እንዲወራረድ ሆኖም ገንዘቡ በሞ/85 በየባለሙያዎች (በየአርቴኸያኖች) ስም በአደራ እንዲቀመጥ፣ሥራው በተገባው ውል መሰረት በቀጣይ እንደሚከናወን፣ የአሰራር ችግር እንኳን ቢያጋጥም አመራሩ ከፍተኛ ክትትል እንደሚያደርግና

ሌሎች ችግሮች ቢከሰቱ መፍትሄ እንደሚሰጥ›› ውሣኔ ያሳለፈ ቢሆንም ይህ ውሳኔ በጥንቃቄ ተግባራዊ ሳያደርግ በመገኘቱ ችግሩ ተከስቷል፡፡

በመሆኑም በዞን ውሃ ሃብት ልማት መምሪያ የባለሙያዎች ቡድን ተቋቁሞ በተደረገው ጥናት መሰረት ከተጠኑት 16 የምንጭ ማጎልበት ሥራዎች ውስጥ 11 የውሃ ጉድጓዶች የማጭበርበር ሁኔታዎች የታዩባቸው መሆኑ በባለሙያ አረጋግጦ በቁጥር 5-2/28/04 በቀን 19/07/04 ዓ.ም ማስረጃ የሰጠና በኦዲት ወቅትም ይኸው በመረጋገጡ ችግር ካለባቸው ከ11ዱ የምንጭ ማጎልበት ግንባታ ሥራዎች ላይ በብልጫ ብር 196,427.30 በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት በአደራ መልክ ሳይያዝ ገንዘቡ አለአግባብ ተከፍሎ ለግለሰቦች ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡

በወረዳው አመራር የተሰጠው አቅጣጫ ራሱ የአሠራር ክፍተት የፈጠረና ቀደም ሲል በተደራጀ መንገድ ስራውን በወቅቱ መፈጸም ይገባው የነበረ ሲሆን ይባስ ብሎም በውሳኔው መሠረት ቢያንስ ገንዘቡ በአደራ ቢያዝ ኖር ለግል ጥቅም ከመዋል ይድን እንደነበር መገንዘብ ተችሏል፡፡ ያም ሆኖ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጥቅምት 20/2006 ዓ.ም ድረስ ስለተወሰደው እረምጃ ምላሽ ባለመሰጠቱ ሁኔታው ያለበትን ደረጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡

22.2 ሰቆጣ ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 17,683.81 በወረዳው ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ቀበሌዎች ለተሰራ የምንጭ ማጎልበት ስራ የሙያ አገልግሎቱን በጨረታ አሸንፈው የግንባታ ዕቃዎችን ከወረዳው ውኃ ሃብት ልማት ጽ/ቤት ወጪ እያደረጉ በመውሰድ ስራውን ካከናወኑ ባለሙያዎች (አርቲዥያኖች) መካከል ለቦታው (ለሳይቱ) በተለያየ ጊዜ ወጪ ካደረጓቸው የግንባታ እቃዎች (ስሚንቶና ቶንዲኖ ብረት) ለስራው መዋል ከሚገባው በላይ ሆኖ የተረፈውን ስራ ላይ በዋለው የትርፍ ዕቃ መመለሻ ቅጽ ላይ አሳንሰው በመሙላትና አንዳንዶቹም ሙሉ ለሙሉ ስራ ላይ እንደዋለ (እንዳልተረፈ) በማስመሰልና ትርፉን ለግል በማስቀረት የመንግስት ሃብት ያለአግባብ ለግል ጥቅም አውለው ተገኝተዋል፡፡

22.3 የመቄት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,345.50 ለግል ጉዳይ ወደ ተለያዩ ውጭ ሃገራት የተደወለበት የስልክ ፍጆታ ከመንግስት በጀት ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ድርጊቱን በፈፀሙት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድና የመንግስት ገንዘብ እንዲመለስ ከማድረግ በተጨማሪ ለወደፊቱም በወጪ ማስረጃ አያያዝና በንብረት አጠባበቅ በኩል ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ በሪፖርት ብናሳስብም ስለተወሰደው እርምጃ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

**አላ□ባብ □ተ□ናመ □ክጸ፣**

23. ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው በኦዲት ሲጣራ በ83 (67%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ወጪ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር **2,210,813.01** አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

አላግባብ ከተከፈለው ክፍያ ከፍተኛውን ድርሻ ከሚይዙት ወረዳዎች መካከል ተንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 355,854.34 አላግባብና በድጋሚ የተከፈለ ውሎ አበል፣ቆቦ ጊራና ሸለቆ ልማት ፕሮግራም ጽ/ቤት ብር 206,923.97 ለጊዚያዊ ኮንትራት ሰራተኞች አላግባብ የተከፈለ የእርከን ጭማሪ፣ ከኮንትራት ወደ ቋሚነት ለተመደቡ ሰራተኞች የተከፈለ የአገልግሎት ካሳ፣መደቡ የሚጠይቀውን የትምህርት ደረጃ ሳያሟሉ ለተመደቡ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ፣ ለመንግስት ስራ ላልዋለ ጊዜ ተከፍሎ የተገኘ ውሎ አበል እና ከስራ ቦታና ሰዓት ውጭ ተከፍሎ የተገኘ የመስተንግዶ ወጪ ይገኙበታል፡፡

ባቲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 115,439.38 አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበልና የስልጠና ወጪ እና ደባርቅ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 108,538.75 አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል እና በፍሉድ በማጥፋት ለሴፍትኔት ተጠቃሚዎች በብልጫ የፀደቀ ወጪ ይገኝበታል፡፡

የ2004 በጀት ዓመት አላግባብ የተከፈለ ክፍያ በ2003 በጀት ዓመት አላግባብ ተከፍሎ ከተገኘው ብር **9,969,278.60** ጋር ሲነፃፀር በብር 7,758,465.59 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡

አላግባብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 352,422.65 (16%) የተተካ ሲሆን ቀሪው 84% ገንዘብ ስለመተካቱ ይህ ሪፖርት እስከተሠራበት ጥቅምት 20/2006 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡

**የግንባታ ክፍያ ሂሳብን በተመለከተ፤**

24. ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ መጀመሪያ ከተያዘው የግንባታ ውል ጋር ባልተጣጣመ ሁኔታ በ35(28%) መ/ቤቶች በድምሩ ብር 41,408,198.12 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት 4 መ/ቤቶች፤

- ጎንደር ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በድምሩ ብር 25,982,384.45 (62.7%) ለከተማ ውስጥ የተፋሰስ ግንባታ፣የተለያዩ የኮብል ድንጋይ መንገድ ንጣፍ ስራዎች ክፍያ ግንባታው በአግባቡ ስለመጠናቀቁ ሳይረጋገጥና የግንባታ ርክክብ ሳይፈፀም የተከፈለ ይገኝበታል፡፡
- እነማይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 3,957,763.02 የማህበረሰብ ኩሬ ውሃ ግንባታ የክፍያ የምስክር ወረቀትና የስራ ዝርዝር ያልቀረበለት፣በገጠር መንገድ ጽ/ቤት ስር ለሚገነባው የሱሃ ድልድይ ግንባታ ከውል በላይ በብልጫ የተከፈለና ስራው መሰራቱ በባለሙያ ያልተረጋገጠ ወጪ ይጠቀሳሉ፤
- የዋግ ኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ነ/ፋይ/ድ/ሰጭ ማዕከል በድምሩ ብር 1,818,991.18 ለቢሮ አገልግሎት የሚውል ባለ4 ፎቅ ህንፃ 4ኛ ዙር ክፍያ ሲፈፀም ለግንባታ የቀረበ እቃ "ማቴሪያል ኦን ሳይት" አለ በሚል ንብረቱ በትክክል ግንባታ ቦታ ላይ ለመኖሩ የባለሙያ ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈፅሞ በመገኘቱ፣
- ሃገረ ማርያም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል በድምሩ ብር 1,888,627.27 ለሙያና ቴክኒክ ማሰልጠኛ ተቋም ግንባታ ክፍያ፣ በየቀበሌው ለተሰሩ የንጹህ መጠጥ ውኃ ግንባታ ምንጭ ማጎልበት፣ የከብት

ማጠጫና የልብስ ማጠቢያ ገንዳ ስራዎች የልኬት ወረቀት (take off sheet) ያልቀረበለት ይይዛል፡፡

ይህም እያንዳንዱ ሥራ በትክክል ስለመሠራቱ በግንባታ ባለሙያ እንዲረጋገጥ ሆኖ ያልተሰራ ከሆነ ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ እና ድርጊቱን በፈጸሙት ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባዉ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

**ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ የወጪ ማስረጃዎች፣**

25. ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ3(2%)መ/ቤቶች ማለትም ደባርቅ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,812,530.43፣ ምስራቅ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 717,772.44፣ ሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 90,424.75 በድምሩ ብር 2,620,727.62 የያዙ የወጪ ቫውቸሮች ከነደጋፊ ማስረጃዎቻቸው ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የወጪዎቹን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በወጪ ማስረጃዎቹ ምን እንደተፈፀመባቸው ብሎም ለማጭበርበር ወንጀል አለመዋላቸው ባለመረጋገጡ ስጋት ያስከተለ በመሆኑ ቀርበው የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ ከማድረግ በተጨማሪ ሰነዶቹን የሰወሩ/ማቅረብ የነበረባቸው ሠራተኞች ተጠያቂ እንዲሆኑ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡ ይሁንና ስለተወሰደው እርምጃ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

**የግዥ ሥርዓትን ያልተከተለ የወጪ ሂሣብ፤**

26. □ክቃና አገልግሎት ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለ□ □ግዥ አዋጅ፤ደንብና መመሪያ መሠረት ስለመፈፀሙ እንዲሁም ጥራትን ሳ□□ □ተሻለ □ክቃ ዃ□ ለመገኘቱና ፍትሃዊ ውድድር የተካሄደ ስለመሆኑ የሚሳዩ የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች □ተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ82(67%) መ/ቤቶች ብር 289,013,714.62 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የግዥ ሥርዓት የሚጠይቀውን መሥፈርት ሣያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡

የግዥ አፈጻፀም ችግር ከታየባቸው መ/ቤቶች መካከል ከ4 ሚሊዮን በላይ የግዥ ሂሳብ የያዙት፡-

- የክልሉ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን ብር 242,723,033.84 (84%) ጨረታ ሳይወጣ የተፈፀመ የተሽከርካሪ ግዥ፤ማሽነሪዎች የተንጓዙበት የአገልግሎት ክፍያ፣የማሽን ኪራይ አገልግሎት ግዥ ፣ከተጠየቀው በላይ የተፈፀመ የቱቦ ማምረቻ ሞልድ ግዥ፤
- የጎንደር ከተማ አስተዳደር ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 9,790,162.15 (3.4%) ግልጽ ጨረታ ሣይወጣ በአካባቢ ማስታወቂያ ብቻ የተፈፀመ የግንባታ ዕቃ ግዥ፣ የግንባታ ክፍያዎች፣ ሽዶችና ድሬኔጅ ግንባታ፤ የተሽከርካሪና የማሽነሪዎች ጥገና፣ ተሽከርካሪና የግንባታ ማቴሪያል የተንጓዛበት እና የደንብ ልብስ ግዥ የተፈጸመበት ክፍያ፣ እና

- ታች አርማጭሆ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 4,623,685.61(1.6%) በአካባቢው ማስታወቂያ ብቻ የተፈፀመ የጽህፈት መሣሪያ፣የኤሌክትሮኒክስና የቢሮ ዕቃዎች ግዥ ክፍያ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ግኝቱ ሊከሰት የቻለውም የግዥ አዋጅ፣ደንብና መመሪያን በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ካለማዋል የተነሣ በገንዘቡ ተገቢዉ ዕቃ (አገልግሎት) መገኘቱን በማያረጋግጥ እና ፍትሃዊ ውድድርን በማያስተናግድ ሁኔታ የተፈፀመ ግዥ መሆኑን በማስገንዘብ ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በኦዲት ሪፖርቶች አሣስበናል፡፡

የ2004 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ተደርጎ የተገኘው የግዥ ሂሳብ ከ2003 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝት ብር 51,688,476.03 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ18 ቢቀንስም በገንዘብ መጠን ግን በብር 237,325,238.59 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ ይህም የግዥ መርህን በአግባቡ በመፈጸም ረገድ ገና በርካታ ችግሮች እንዳሉ ያለመክታል፡፡

**የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ውጤት፣**

**የንብረት ሂሳብን ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች፣**

27. መንግሥት ለዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በአብዛኞቹ የክልሉ መ/ቤቶች የሚታየው የንብረት አያያዝና አስተዳደር በኦዲት ለማረጋገጥ በሚያስችል ደረጃ ባለመገኘቱ የሙያ ምስክርነት ለመስጠት አስተማማኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት የመንግስት ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የተጋለጠ ሲሆን ደህንነቱንም በኦዲት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

    መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና ከዚያ ወዲህ ስለንብረት አያያዝና አጠባበቅ የተሻሻሉ መመሪያዎች በሚያዙት መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 98 መ/ቤቶች መካከል በ43(44%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ለዚህም ምክንያቶቹ:-

    - አላቂና ቋሚ ዕቃዎች በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሚቆጠርበት ወቅት በገቢና በወጪ እንዲሁም በመዛግበት ላይ ተገቢው መተማመኛ ፊርማ እየተፈረመ ውጤቱ ሪፖርት ስለማይደረግና በመከታተያ መዝገብ ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር በመሆኑ፣
    - የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ (ካርዶች) ባለመቋቋሙና ቢቋቋምም ምዝገባ በተሟላ መልኩ ባለመከናወኑ፣
    - የንብረት ክፍል ሰራተኞች ሲቀያየሩ የተሟላ ርክክብ የማይደረግ በመሆኑና ርክክብ ሲደረግም የርክክቡ ቀን ተገልጾ በመዛግብቶችና የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች ላይ መለያ ምልክት አለማድረግና አለመፈራረም የሚሉት ዋና ዋና ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም የተጠቀሱትን የንብረት አያያዝና አስተዳደር ችግሮች በማረም ሊከሰት የሚችለውን የመንግስት ንብረት ብክነት እንዳይከሰት ተገቢው የንብረት አስተዳደር፤አያያዝና አጠቃቀም በየመ/ቤቱ እንዲጠናከር በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡

**የወረኢሉ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት የግንባታ ዕቃዎች ሂሣብ ጉድለት ብር 65,114.70፤**

28. የወረኢሉ ወረዳ ምክር ቤት ለመ/ቤታችን በደብዳቤ ቁጥር አፈ-ጉ/17/05 በቀን 23/02/05 በሰጠው ጥቆማ የቀድሞ የትምህርት ጽ/ቤት ንብረት ክፍል ሰራተኛ የነበሩት ከህዳር 28/1999 እስከ ግንቦት 08/2001 ዓ.ም ድረስ ካንቀሳቀሱት የግንባታ ዕቃዎች ሂሳብ በተለያዩ የማጭበርበር ስልቶች በመጠቀም ለግል ጥቅም የዋለ ብር 55,807.50 እና የተለያዩ የንብረት በስማቸው ያንቀሳቀሱ ሠራተኞች የንብረት ሂሳብ ሲመዛዘን በጉድለት ብር 9,307.20 ተገኝቷል፡፡ ከማጭበርበር ስልቶቹ በጥቂቱ፡-

- በራሪና ቀሪ የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) በመደለዝ፣ ማበላለጥና ደረሰኙ ከተዘጋ በኋላ በቀሪው ላይ ቁጥር በመጨመር በ15 የግንባታ ዕቃዎች ላይ የማጭበርበር ተግባር በመጠቀም ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ በድምሩ ብር 14,745.00 መገኙቱ፣
- ስምና ፊርማ በማመሳሰል ወጪ እንደተደረገ ሆኖ ለግል ጥቅም የዋለ የቤት ክዳን ቆርቆሮ፣ሚስማርና ሲሚንቶ ሂሳብ ብር 27,870.00፣
- ንብረት ወጪ ባላደረገና በማይታወቁ ግለሰቦች ስም ወጪ የተደረገ በማስመሰል የተወሰደ ስሚንቶ፣ጀሶ እና የግድግዳ ቀለም ሂሳብ ብር 4,675.00 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ይህም የተጣለባቸውን እምነት በማጉደል ዕቃዎችን ለግል ጥቅም ለማዋል በተለያየ ዘዴ የተደረገ የማጭበርበር ተግባር በመሆኑ በህግ እንዲጠየቁና ንብረቱን እንዲተኩ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርቱ የተላለፈ ቢሆንም እስካሁን ምን ደረጃ እንደደረሰ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡

**በገንዘብ የማይገለፁ በልዩ ኦዲት የተከናወኑ የኦዲት ስራ ውጤቶች፣**

29. በተለያዩ አካላት በቀረበው ጥቆማ መሰረት ከተከናወኑት የ10 የልዩ ኦዲት ሥራዎች በገንዘብ የተገለፁ ግኝቶች በዚህ ሪፖርት ውስጥ በየሚመለከታቸው ርዕስ የተካተቱ ሲሆን በገንዘብ መገለፅ ያልተቻሉት የ2 መ/ቤቶች ተጨማሪ ግኝቶች ደግሞ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**የቆቦ ጊራና ሸለቆ ልማት ፕሮግራም ጽ/ቤት፤**

29.1 ለኦዲቱ ሥራ መነሻ የሆነው በሰሜን ወሎ ዞን በራያ ቆቦ ወረዳ ለሚገኘው የቆቦ ጊራና ሸለቆ ልማት ፕሮግራም ጽ/ቤት የተመደበው ሃብት፣የተከናወኑ ተግባራትና የተገኙ ውጤቶች በስራ አመራር ቦርድ እና አጠቃላይ ሰራተኞች ሲገመገሙ በተስተዋሉ ጉዳዮች ምክንያት የሃብት አያያዝ፤አጠቃቀምና የስራ አፈፃጸሙ በልዩ ሁኔታ ኦዲት እንዲደረግ ከመስተዳድር ምክር ቤት ጽ/ቤት እና ከፕ/ጽ/ቤቱ ስራ አመራር ቦርድ በተጠየቀው መሰረት ነው፡፡ የቀረቡት ዝርዝር ጥያቄዎች በኦዲት ሲጣሩ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- **በቋሚነት አንድን ተጫራች ተጠቃሚ የሚያደርግ መስፈርት መዘጋጀቱን በተመለከተ፤**

  ከ1996 እስከ 2001 ዓ.ም ድረስ ፕሮግራም ጽ/ቤቱ ካከናወናቸው የመስኖ ስራዎች መካከል የጉድጓድ ቁፋሮ፣ ፓምፕ አቅርቦትና ተከላ፣ የኤሌክትሮ መካኒካል ዕቃዎች ግዥና የመስኖ አውታር ዕቃዎች አቅርቦትና ዝርጋታ ስራ በአብዛኛው በአንድ ቻይና ጂኦ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ) በተባለ ድርጅት የተከናወነ እንደሆነና ይህን ድርጅት ለመምረጥም ፕሮግራም ጽ/ቤቱ ሲጠቀምበት የቆየው የጨረታ መገምገሚያ መስፈርት ሲታይ ‹‹በክልሉ ያለው የስራ ልምድ፣ በራያ ሸለቆ አካባቢ ያለው የስራ ልምድ እና የመጫረቻ ሰነዱን ያሞገሰ፤በተመሳሳይ ፕሮጄክቶች የሰራ››በሚል የተዘጋጀ በመሆኑ አዳዲስ ተወዳዳሪዎች እንዳይገቡ የገደበና በተጠቀሱት ጊዜያት የጨረታ ማሥታወቂያ ሲወጣ በቴክንክ ዉድድር በእነዚህ መስፈርቶች ምክንያት ይህ ድርጅት ሙሉ ነጥብ ሲያገኝ ሌሎች ዜሮ እያገኙ የሚሸነፉበት ሁኔታ የተፈጠረ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

  ሌላዉና አፈጻጸሙ ተጨማሪ ችግር እንዳለበት የሚያመለክተው ይህ በተከታታይ አሸናፊ የተደረገዉ ድርጅት ህጋዊ የፖምፕ አቅርቦት እና ተከላ እንዲሁም የመስኖ አውታር እቃዎች አቅርቦትና ዝርጋታ ህጋዊ የሙያ ፍቃድ ሳይኖረው ከጠቅላላ ብር 42,800,918.77 ግዥ ውስጥ የብር 21,594,949.87 በተገለጸው የማወዳደሪያ የቴክኒክ መስፈርት መሠረት እየተመረጠ አቅርቦት ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

  ይህ ድርጊት በፕ/ጽ/ቤቱ ስራ አመራሮችና በኮርፖሬሽኑ መካከል አንዳች ትስስር ሊኖር እንደሚችል አመላካች ነው፡፡ ስለሆነም የቀድሞው ስራ አስኪያጅ እና ሃይድሮሎጅስቱ በህግ ተጠያቂ ሊሆኑ እንደሚገባ የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

- **አማካሪ ድርጅት ሳይኖር በአሰሪና በተቋራጩ ስምምነት ብቻ የተተገበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ፤**

  ከቻይና ጅኦ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን-ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ (CGC) ከተባለ ድርጅት እና አግሪ ቴክ ሲስተምስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ጋር የጉድጓድ ቁፋሮና ፓምፕ ቴስት፣ ኬዚንግ አቅርቦትና የመስኖ አውታር ዝርጋታ ስራ ሲከናወን በመስፈርቱ መሠረት ስለመቅረቡና ስራዎችን በጥራት መሰራታቸውን እያማከረ በማረጋግጥ ክፍያ እንዲፈጸም የሚያደርግ ብቃት ያለው ባለሙያ ሳይኖር (ያለአማካሪ) በፕሮግራም ጽ/ቤቱ ብቻ ይከናወን እንደነበር ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

  በዚህም ምክንያት የቻይና ጅኦ ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን(የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ) ከቆፈራቸው ጉድጓዶች መካከል አንዳንዶቹ አሸዋ (ሲልት) ብቻ የሚያወጡ እንደሆነ በቀረበው ጥቆማ መሰረት ለማረጋገጥ የባለሙያ ድጋፍ ከአማራ ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ትብብር ተጠይቆ አስፈላጊ የሆኑ የውል ሰነዶችን፣ የቁፋሮ ክትትል ሪፖርትን በመገምገም፣ በመስክ በመገኘት የጉድጓዶችን የውሃ ጠለል እና የተገጠሙ የኬዚንግ ውፍረት የመለካት እንዲሁም ከጉድጓዱ የሚወጣውን ውሃ የድፍርስነት ሁኔታ የመገምገም ስራዎች በባለሙያ ተሰርተዋል፡፡

በዚሁ መሠረት ከጉድኀዶቹ አንዱ የሆነው ሆርማት ጎሊና ቁጥር 19 ውስጥ የገባው ኬዚንግ (የውሃ ማጣሪያ) ስምምነቱ ላይ በተጠቀሰው መስፈርት (ስታንዳርድ) መሰረት ለ12 ኢንች በ9 ሚ.ሜ ውፍረት ያለው መሆን ሲገባው በ6 ሚ.ሜ ውፍረት ሆኖ መገኘቱን ህዳር 3/2005 ዓ.ም በተፃፈው የባለሙያ ትንተና የያዘ ሪፖርት ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም በውሉ ላይ በተመለከተው መጠን ሳይሆን ዝቅተኛው ሲቀርብ በወቅቱ ክትትል ሲያደርጉ የነበሩት ባለሙያ የቀረበው ኬዚንግ በውሉ መሰረት ነው ብለው በማረጋገጣቸውና ክፍያው እንዲፈፀም በማድረጋቸው እንዲሁም፤

አቅራቢው ድርጅትም በውሉ መሰረት ማቅረብ የነበረበትን ኬዚንግ ሳያቀርብ ከሚፈለገው መጠን በታች ላቀረበው ዕቃ በውሉ የዋጋ መጠን እንዲከፈለው በመጠየቁና ክፍያውንም በመውሰዱ ለተፈጠረው የውሃ ጥራት መጓደል በህግ ተጠያቂ ሊሆኑ የሚገባ ሲሆን በወቅቱ የነበረው የ2ቱ ኬዚንግ የዋጋ ልዩነት ተጠንቶ ገንዘቡ ድርጊቱን ከፈፀሙት ባለሙያ እና ከቻይና ጂኦ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ኢትዬጵያ ቅርንጫፍ) ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርቶቻችን አስገንዝበናል፡፡

በተጨማሪም የሙያ ምስክርነት እንዲሰጥበት ለአማራ ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ተልኮ ውጤቱ እየተጠበቀ የሚገኝ ‹‹እንዲገዛ ተጠይቆ የነበረው ቀርቶ የጥራት ችግር ያለበት ፍላት ድሪፐር ተገዝቷል›› የተባለው ጥቆማ በባለሙያ እንዲጣራ ለአማራ ዲዛይና ቁጥጥር ድርጅት ቢላክም የተደረሰበት ውጤት በወቅቱ ለመ/ቤታችን ባለመድረሱ የባለሙያ ማረጋገጫ ማስረጃውን የክልሉ ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በዚያው በኩል ተከታትሎ መቀበል የሚችል መሆኑን በሪፖርታችን አሳሰበናል፡፡

በስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን በኩል ባጠቃላይ የፐ/ጽ/ቤቱን ግኝቶች አስመልክቶ በዝርዝር በቀረቡላቸው ሪፖርቶች ላይ ስለተወሰደው እርምጃ አንድ በአንድ የሚገልጽ ግብረ-መልስ ሳይሆን በዚህ ሪፖርት ገጽ 10 ተራ ቁጥር 16.3 ስር የተገለጸውን አጠቃላይ ምላሽ በመሰጠቱ በእነዚህ ግኝቶች ላይ የተወሰደውን እርምጃ ለይቶ ማወቅ አልተቻም፡፡

**የገለጎ ከተማ ማዘጋጃ ቤት**

29.2 ኦዲቱን ለመስራት መነሻ የሆነው ከአካባቢው ተቆርቋሪዎች የቀረበው በጥቅሉ በቋራ ወረዳ በገለጎ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የተመደበው ሀብት፣የተከናወኑ ተግባራትና በከተማ ቦታ አሰጣጥ ዙሪያ የአሰራር ችግሮች መኖራቸውን ለመ/ቤታችንና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በቀረበው ጥቆማ መሰረት ሲሆን ጥቆማው በኦዲት ሲጣራ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- **የፕሮቶኮል መዝገብ፤የመሬት ይዞታ መዛግብት እና የገቢ ደረሰኞችን አያያዝ ችግር በተመለከተ፤**

በማዘጋጃ ቤት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ (መ/ሂ) እንዲጠፋ እንዲሁም ፕሮቶኮል መዝገብ በፍሉድ እንዲደለዝ መደረጉና ቀሪ ደብዳቤዎች እንደተቃጠሉ በቀረበው ጥቆማ መሰረት ማጣራት ሲደረግ፤

- በ2003 ዓ.ም ፕሮቶኮል መዝገብ ላይ ተራ ቁጥር 110 የተሰረዘ፣84፣148፣165፣ 295፣314፣ 341፣345 በፍሉድ የጠፋ እንዲሁም በ2004 ዓ.ም መዝገብ ላይ ተራ ቁጥር 538፣579፣726፣ 995 በፍሉድ እንዲጠፉ መደረጉ ተረጋግጧል፡፡
- ከዚሁ መዝገብ የተያያዙ ብዛት ያላቸው ደብዳቤዎች በፍሉድ እየጠፉና እየተሰረዙ መሰራቱና በኮሚቴ ተጣርቶ የተመዘገበው የህዝብ ቦታ ይዞታ መዝገብ ራሱ እንዲጠፋ መደረጉ፤
- የገቢ ማጠቃለያ ደረሰኝ መ/ሂ-64 አንድ ጥራዝ መጥፋቱ፤ የማዘጋጃ ቤቱ ስራ አስኪያጅ የነበሩት መዛግብትና ሰነዶችን ሳያስረክቡ መሄዳቸው፤
- በተመሳሳይ ቀን እና የደብዳቤ ቁጥር ሶስት የትክ የመኖሪያ ቦታ ደብዳቤዎች (አንዱ ተሽሯል ይላል) የማዘጋጃ ቤቱ ስራ አስኪያጅ በነበሩት በቁጥር መ/ማ/192/03 በቀን 22/10/03 ወጪ ተደርጎ 3 የተለያየ ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ቦታ በደብዳቤ ተሰጥቶ ተገኝቷል፡፡

ይህም በጥቅማው የቀረቡ ችግሮች እንደተፈጸሙና መረጃን ለማጥፋት ታስቦ የተደረገ ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የማዘጋጃ ቤቱ የመዝገብ ቤት ሰራተኛ የነበሩት ከቀድሞ ስራ አስኪያጅ ጋር ሆነው መረጃዎችን በመሰረዝ፣በማጥፋት እና የተጣለባቸውን ሃላፊነት ለግል ጥቅም በማዋላቸው በህግ ሊጠየቁ እንደሚገባ እንዲሁም የሂሳብ ኦፊሰር የነበሩት አንድ ጥራዝ የገቢ ማጠቃለያ ደረሰኝ (መሂ/64) ያጠፉ እና ስለመጥፋቱም ለሚመለከተው አካል በጽሁፍ ያላሳወቁ በመሆኑ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድባቸው እንደሚገባና ደረሰኙ ተፈልጎ ሊቀርብና ወንጀል ተፈጽሞበት ከሆነም ተገቢው ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በሪፖርታችን በዝርዝር አስገንዝበናል፡፡ ሆኖም ስለተወሰደው እርምጃ እስከ ጥቅምት 20/2006 ዓ.ም የተሰጠ ግብረ መልስ አልደረሰንም፡፡

- **በዚሁ ኦዲት ወቅት በተጨማሪ ያጋጠሙ የመረጃ አቅርቦት ችግሮች፡-**

  የይዞታ አጣሪ ኮሚቴ ስለማቋቋም፤ በማዘጋጃ ቤት/በንዑስ ማዘጋጃ ቤት ደረጃ/ የሚመለከታቸውን አካላት የያዘ አጣሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ መስራት እንዳለበት የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ መመሪያ በሚያዘው መሰረት የይዞታ አጣሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ እንዲሰራ የተደረገ ቢሆንም የይዞታ ቦታ መዝገቡ እንዲጠፋ በመደረጉ ለኦዲት ሊቀርብ አለመቻሉ፣

  በዞን ስራና ከተማ ልማት መመሪያ አማካኝነት የትክ ቦታ ይዞታ አጣሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ እንዲሰራ ቢደረግም በኮሚቴው ተሰርቶ የቀረበው ዝርዝር ሰነድ በኮሚቴው ባለመፈረሙ የመረጃውን ህጋዊነት የማይገልጽ መሆኑ፤

  የከተማ ምሪት የቦታ ሽንሽና ጥናት ዝርዝር ማስረጃ ለኦዲት አለመቅረቡ (መጥፋቱ) እና ትክ ቦታ የተሰጣቸው ነዋሪዎች ወደ ቦታቸው የሄዱ ስለመሆኑ የሚያሳይ የክትትል ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ መሆኑ፤በኦዲት ወቅት ያጋጠሙን ዋና ዋናዎቹ ችግሮች ናቸው፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባኤ!**
**የተከበሩ ፕሬዚዳንት!**
**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**
**ክቡራትና ክቡራን!**
**የማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶችን ከዚህ ቀጥሎ አቀርባለሁ!**

**ማጠቃለያ፣**

30. በዚህ አጭር ሪፖርት የውስጥ ክፍሎች በዝርዝር እንደተመለከተው በ2004 በጀት ዓመት ሂሳቦች ላይ በተደረገው ኦዲት በጥሬ ገንዘብ ጉድለት መጠን፤ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ፤ አላግባብ የተሰፈጸመ ክፍያ መጠን በተመለከተ ካለፉት ዓመታት የተሻለ ነው ቢባልም ያልተሰበሰበ (ውዝፍ) ገቢ፤የግዥ ስርዓትን ያልጠበቀ ግዥ፤የማጭበርበር ወንጀል የተፈጸመበት ገቢና ወጪ ሂሳብ ሲታይ ጉልህ ግኝቶች ተስተውለዋል፡፡ በጥቅሉ ከ2000 እስከ 2004 ያሉት 5 በጀት ዓመታት ሂደቱ ሲገመገም በተወሰኑት ግኝቶች ላይ መሻሻል ቢታይም በአንዳንዶች ግኝቶች ላይ መሻሻል አልታየም ማለት ይቻላል፡፡

**ጥሬ ገንዘብን በተመለከተ፤**

31. በ51 መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2004 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ሲሆን ኦዲት በተደረጉት ሌሎች 5 መ/ቤቶች የቀድሞ ገንዘብ ያዦች ላይ ቷቅላላ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 709,701.20 ተገኝቶባቸዋል፡፡

- በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በጥሬ ገንዘብ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ7 መ/ቤት ብር **1,248,454.47 የለጀር ከወጪ ቀሪ** በመብለጥ (የጥሬ ገንዘብ በማነስ) የተስተውሏል፡፡

**የገቢ ሂሳብን በሚመለከት**

32. የመንግስት ገቢ በወቅቱና በአግባቡ ተሰብስቦ ለታለመለት ዓላማ መዋል ያለበት ቢሆንም በ2005 በጀት ዓመት ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች መካከል በ7 መ/ቤቶች ብር 155,947.53 በተጭበረበረ መንገድ ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም በወቅቱ ተሰብስቦ ስራ ላይ መዋል የነበረበት ከተለያየ ምንጭ የሚገኝ ያልተሰበሰበ (ውዝፍ) ገቢ መኖሩ ታውቋል፡፡

**የወጪ ሂሳብን በሚመለከት፤**

33. የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብ ማጭበርበር የተፈጸመበት ክፍያ መጠን ከ2003 በጀት ዓመት ከተጭበረበረው ጋር ሲነፃፀር ከመሻሻል ይልቅ የተባባሰ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
በተመሳሳይ አንድ ዓይነት ቁጥር ባለለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ለ2 ጊዜ ተሰብስቦ ለመንግስት ፈሰስ መደረጉ ያልተረጋገጠ ሂሳብ በተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብና ሰነድ በመሰረዝና በመደለዝ በተጭበረበረ መንገድ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ተስተውሏል፡፡

የቀን ሠራተኞች ሥራ ላልሠሩባቸው ቀናት እና ሥራ በለቀቁ ሠራተኞች ስም ሀሰተኛ ሰነድ እየተዘጋጀ ክፍያ እንደተፈፀመ ተደርጎ ገንዘብ በኃላፊዎች ለግል ጥቅም መዋሉ ተረጋግጧል፣

በአዲስ ያልተሰሩ የመጠጥ ውሃ ተቋማት የሥራ ዝርዝሮች (ስትራክቸሮችን) አዲስ እንደተሰሩ ተደርጎ ርክክብ መደረጉና ክፍያዎች መፈጸማቸው ተስተውሏል፡፡

የ2004 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገዉ የግዥ ሂሳብ ከ2003 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝት ብር ጋር ሲነፃፀር ከግዥ መርህና አሠራር በወጣ መንገድ የተፈጸመው ግዥ ጨምሮ ተገኝቷል፡፡

**የንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅና አጠቃቀምን በተመለከተ፤**

34. የክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፤ደንበና መመሪያ በሚያዘው መሠረት አብዛኞቹ መ/ቤቶች በተለይ በቋሚና አላቂ ዕቃዎች ላይ አግባብ ያለው የንብረት አያያዝ አመዘጋገብና የቁጥጥር ሥርዓት በመተግበር ክትትል ባለመደረጉ የንብረት ሂሳብ ኦዲት አድርጐ አስተያየት ለመስጠት አለመቻሉ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ዓበይት ጉዳዮች ናቸው፡፡

35. በሌላ በኩል በተከበሩ የክልሉ ም/ቤት አፈ-ጉባኤዎችና ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት በተሰጠው ትኩረት የሚመለከታቸው አካላትን ያካተተ የጋራ ግብረ ሃይል ተቋቁሞ ለግኝቶች እርምጃ አወሳሰድ መሥራት መጀመሩ በእርምጃ አወሳሰዱ ላይ የበኩሉን ዕገዛ እያደረገ ሲሆን የበለጠ እንዲጠናከር ትኩረት የሚያስፈልገው ሆኖ፤

በዚሁ የተቀናጀ ጥረትም ከ2002 እስከ 2004 ባሉት 3 ዓመታት ለተከበረው ም/ቤት ሪፖርት ቀረቦባቸው በነበሩ የገንዘብ ጉድለትና/ማጭበርበር የተፈጸመባቸው ግኝቶች ላይ በተደረገው ክትትልና ከፍትህ አካላት በተገኘው ግብረ መልስ መሠረት ከ3ቱ ዓመታት በድምሩ ብር 701,108.12 ከየሚመለከታቸው መሰብሰቡን፤ብር 4,300,976.07 ላይ ክስ ተመስርቶ በክርክር ሂደት ላይ መሆኑና በሌሎች ላይ ደግሞ በወንጀል ክስ ተመስርቶ ከ1 እስከ 9 ዓመት ጽኑ እስራትና ከብር 500.00 እስከ ብር 10,000.00 የገንዘብ ቅጣት በተለያዩ አጥፊዎች ላይ ተወስኖ ተፈጻሚ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ (ዝርዝሩን ከአባሪዎቹ ይመለከቱ)፤

**የተከበሩ አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበሩ ፕሬዚዳንት!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**ከዚህ ቀጥሎ የማሻሻያ አስተያየቶች አቀርባለሁ፤**

በዚህ ዓመት የኦዲት ሪፖርቶች ከተስተዋሉ ግኝቶችና ከላይ ከተሰጠው ማጠቃለያ ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና ሌሎች ሀብቶችን አመራር ለማጠናከር የሚከተሉትን የማሻሻያ አስተያየቶች እናቀርባለን፡፡

36. **በጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ላይ ቁጥጥሩን ማጠናከር ስለማስፈለጉ**

ከግኝቶች መረዳት እንደተቻለው በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በተለያዩ ምክንያቶች ማመዛዘን ያልተቻለ ሲሆን ይህም የመንግስትን ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ የሚዳርግ በመሆኑ በየመ/ቤቱ የሚገኙ ሥራ አመራሮችና የውስጥ ኦዲተሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል፡፡

37. **የገቢና ወጪ ሂሳብ ማጭበርበሪያ ክፍተቶችን በአሠራር ስርዓት ስለመዘርጋት፤**

በገቢና በወጪ ሂሣብ ላይ ለተከሰቱ የማጭበርበር ድርጊቶች ክፍተት የፈጠሩ አሠራሮችን እየፈተሹ በመድፈንና የፈጻሚዎችንና አመራሮችን አቅም በመገንባት የመንግስት ሃብትን በአግባቡ ይዞ መጠቀም እንዲቻል ማድረግና የፍትህ አካላትም በአጥፊዎች ላይ አስተማሪ የሆነ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል እንላለን፡፡

38. **የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ መጠናከር የሚገባው ስለመሆኑ፤**

በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ተቋቁሞ የማይሠራባቸውና በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ የማይከናወን በመሆኑ የንብረት አያያዝና አጠባበቅን ኦዲት አድርጐ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ስለሆነ መ/ቤቱቹ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ በማቋቋምና በየጊዜው ቆጠራ እያከናወኑ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪው ጋር እያመሳከሩ ልዩነት ሲፈጠርም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ ሊሰሩ ይገባል፡፡

39. **በየደረጃው ያሉ የህዝብ ምክር ቤቶች በኦዲት ሪፖርት ላይ ክትትል ሊያደርጉ ያስፈልጋል፡፡**

በየደረጃው የሚገኙ ም/ቤቶች ለየአካባቢያቸው በሚደርሰው የውጭ እና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች በክልሉ ም/ቤት እንደሚደረገው ሁሉ በተለያዩ የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች (በተለይም በበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ) አማካኝነት ለየም/ቤቱ ጉባኤ በአጀንዳነት ቀርቦ ውይይት ሊደረግበትና አቅጣጫ እየሰጠበት ክትትሉ ሊጠናከር ይገባል እንላለን፡፡

40. **ባለፈው ዓመትም ቀርቦ መፍትሔ ያላገኘውን ልማቱ የፈጠራቸው አዳዲስ መ/ቤቶችን በተመለከተ፤**

መ/ቤታችን የኦዲት ሽፋንን ለማሣደግ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና ለክልሉ ከሚመደበው በጀት አንፃር የተቻለውን ሽፋን እየሰጠ ቢሆንም የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ቁጥር በየጊዜው በመለዋወጡና በመጨመሩ ምክንያት በታሰበው መሠረት በቁጥር ደረጃ ሽፋን እየተሰጠ አለመሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

ለዚህም ምክንያቱ በጀታቸው በተነጻጻሪ ደረጃ አነስተኛ ቢሆንም እንደ ጤና አጠባበቅ ጣቢያዎችና የወረዳ ፍርድ ቤቶች ያሉ መ/ቤቶች ሂሣባቸውን ራሳቸውን ችለው ስለሚይዙና እንደ አንድ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤት ስለሚቆጠሩ የኦዲት ተደራጊውን መ/ቤት ቁጥርን ከ1500 በላይ አድርሰውታል፡፡ በመሆኑም፣

- በጀታቸውን ጤና ጥበቃ ቢሮ የሚይዝላቸው በየዓመቱ ቁጥራቸው እያደረ የመጣው ጤና አጠባበቅ ጣቢያዎችን የሂሣብ እንቅስቃሴ አማክሎ የሚከታተል በየወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በፑል ተደራጅተው የጋራ አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ቢኖር፣
- በጀታቸውን ሠራተኛና ማህ/ጉዳይ ቢሮ የሚይዝላቸው የአካል ተሃድሶ ማዕከላት ሂሳብ ለቢሮው ሪፖርት ሲያቀርቡ የሂሣብ ማስረጃዎችንም እንዲያስረክቡ የሚደረግበት ሁኔታ ቢመቻች፣
- በጀታቸውን ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚይዝላቸው በዞንና በወረዳ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች የሂሣብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ስራቸው ላይ ተጽዕኖ በማያመጣ መልኩ በየአቅራቢያቸው በሚገኝ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል በኩል ሂሳባቸው ተጠቃሎ የሚያዝበት ሁኔታ ቢኖር፣
- በጀታቸውን የክልሉ ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን የሚይዝላቸው ማረሚያ ቤቶች ሂሣብ በየአቅራቢያቸው የነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጪ ማዕከል ተጠቃሎ የሚያዝበት ሁኔታ እንዲጠናና ተግባራዊ እንዲሆን አስተያየታችንን እናቀርባለን፡፡

41. የኦዲት ተደራሽነትና ጥራት እንዲሁም የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የምስራቅ አማራን የሚሸፍን ደሴ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትን ለመክፈት ያቀረብነው የመዋቅር ማሻሻያ ጥያቄ አውንታዊ ምላሽ ያገኘ በመሆኑ የሰው ሃይል ደረጃና ቁጥር በማስወሰን ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግባት በዝግጅት ላይ እንገኛለን፡፡
42. ከዚህ ጋር በተያያዘ ልምድ ያለው ሠራተኛ ፍልሰትን ለመቀነስ ከሌሎች አቻ ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ክፍያ ጋር በማነጻጸር ካቀረብነው የጥቅማ ጥቅም ማሻሻያ ጥያቄ መካከል የመዘዋወሪያ አበል ማሻሻያ ብቻ የተፈቀደ ሲሆን ከቀረበው ጥያቄ አንጻር ውስን በመሆኑ በሌሎች ጥያቄዎች ላይም አዎንታዊ ምላሽ ቢሰጥባቸው ህዝብና መንግስት ከኦዲት ሙያው ተጠቃሚ እንደሚሆን እምነቴን እየገለጽኩ!!

በመጨረሻም የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤዎች፣ የበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ኮሚቴዎች፣ የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሥራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እንዲሁም የመ/ቤቱ ባለሙያዎችና መላው ሠራተኞች ደግሞ በዚህ ሪፖርት ለተገኙት ውጤቶች ላሳዩት ቅንጅት፤ታታሪነትና ላላቸው መልካም ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋና እያቀረብኩ ሪፖርቴን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡ አመሰግናለሁ!!

ደሴ ጥላሁን አያሌው
ዋና ኦዲተር
የካቲት /2006
<u>ባህር ዳር፤</u>